የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# ፓርላማ ዜና መጽሔት

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን በሰኔ ወር መደበኛ ጉባኤውን እና ልዩ ሰብሰባውን አካሂዷል፡፡ የሰኔ ወር ዜና መጽሔታችንም በተካሄዱት መደበኛ ጉባኤዎችን የወጡ አዋጆችንና የተላለፉ ውሳኔዎችን፣ የተደረጉ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎችን አስመልክቶ በአጭሩ ለማቃኘት እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

## ዓበይት ርዕሶች

- ሕግ አወጣጥ
- ክትትል ቁጥጥር

መልካም ንባብ!
ሰኔ፤ 2018 ዓ.ም

# ሕግ አወጣጥ

6ኛው የኢ.ፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ሰኔ 2 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 24ኛ መደበኛ ጉባኤው የጉምሩክ አዋጅን እንደገና ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ አዋጅ እና የቁልፍ መሠረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ረቂቅ አዋጅን መርምሮ አፅድቋል፡፡






ምክር ቤቱ በውሎው የጉምሩክ አዋጅን እንደገና ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ አዋጅን የፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ ደሳለኝ ወዳጆ ሪፖርት እና የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡

ሰብሳቢው እንደገለጹት ረቂቅ አዋጁ በዘርፉ ሀገራችን ከፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን የሚያስችል

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

ሲሆን፣ በጉምሩክ አሠራር ውስጥም ፍትሃዊነት እንዲረጋገጥ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ፣ ረቂቅ አዋጁ በሀገራችን እያደገ የመጣውን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት የሚደግፍ እና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ መሆኑን፣ አስመጪዎች በቀረጥና ታክስ አወሳሰን ላይ ያላቸውን አቤቱታ በማቅረብ ሂደት ያጋጥሟቸው የነበሩ የአሠራር መሰናክሎችን ለማስወገድ የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን ያካተተ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ፣ የጉምሩክ አዋጅን እንደገና ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1425/2018 አድርጎ በሁለት ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል፡፡

በተያያዘም ምክር ቤቱ የቁልፍ መሠረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ረቂቅ አዋጅን አስመልክቶ የውጭ ግንኙነትና የሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ዲማ ነጎዎ (ዶ/ር) ሪፖርትና የውሳኔ ሐሳብ ለምክር ቤቱ በንባብ አሰምተዋል፡፡






አክለውም ሰብሳቢው የሳይበር ደህንነት ፕሮግራሞችን ለማስፈጸም፣ ለሥልጠና፣ ለምርምርና ለቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ የሚውል ራሱን የቻለ የቁልፍ መሠረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ፈንድ በአዲስ ምዕራፍ መደንገጉንም አስረድተዋል።

በአዋጁ አፈጻጸምና በቅጣት አወሳሰድ ላይ በመንግሥትና በግል ተቋማት መካከል የነበረው ልዩነት ተሰርዞ አዋጁ በመንግሥትም ሆነ በግል ቁልፍ መሠረተ ልማቶች ላይ እኩልና ፍትሐዊ ተፈጻሚነት እንዲኖረው የሚያደርግ መሆኑ አብራርተዋል፡፡

ማንኛውም የመሠረተ ልማት ባለቤት፣ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሆነ ብሎ ጥፋት ካጠፋ በሕግ ይጠየቃል ያሉት ዲማ (ዶ/ር) በሌላ በኩል ደግሞ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ወቅታዊ የደህንነት ሁኔታዎችንና የሳይበር ጥቃት ስጋቶችን ለሕዝብ ይፋ የማድረግ ግዴታ ተጥሎበታል ብለዋል።



ምክር ቤቱ በረቂቅ አዋጁ ላይ በጥልቀት ከተወያየ በኋላ ረቂቅ አዋጁ አዋጅ ቁጥር 1426/2018 አድርጎ በሙሉ ድምፅ አጽድቋል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የስራ ዘመኑ ሰኔ 18 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 28ኛ መደበኛ ጉባኤው የመረጃ ነፃነት ረቂቅ አዋጅ እና ለማጽደቅ የቀረበውን ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ እውነቱ አለነ ለምክር ቤቱ በንባብ አቅርበዋል፡፡






የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የስራ ዘመኑ ሰኔ 18 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 28ኛ መደበኛ ጉባኤው የመረጃ ነፃነት ረቂቅ አዋጅ እና ለማጽደቅ የቀረበውን ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ እውነቱ አለነ ለምክር ቤቱ በንባብ አቅርበዋል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ እውነቱ አለነ ሪፖርቱን ባቀረቡበት ወቅት የምክር ቤት አባላት በጋዜጠኞች መብት፣ በመረጃ አሰጣጥ ወጪዎች እና በሀገር ሚስጥር መግለጥ ቅጣቶች ዙሪያ ጥያቄዎችን አንስተው ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡-

የጋዜጠኞችና የዜጎች መረጃ የማግኘት መብት ጋዜጠኞች ለሕዝብ ጥቅም የሚውሉ መረጃዎችን ያለምንም ክፍያ ማግኘት እንደሚችሉና ሌሎች መረጃ ጠያቂዎች ደግሞ ሰነዱን ለመገልበጥ (ፎቶ ኮፒ) የሚያስፈልገውን ወጪ ብቻ በመሸፈን መረጃ ማግኘት እንደሚችሉ ሰብሳቢው አብራርተዋል።

የሀገር ሚስጥርና የቅጣት ሁኔታ ሚስጥራዊ መረጃን አሳልፎ ለሰጡ አካላት የተቀመጠው ቅጣት  አነስተኛ ሆነ ተብሎ  ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረበው ጥያቄ  በአዲሱ አዋጅ የተካተቱት በሀገሪቱ የወንጀል ሕግ ያልተሸፈኑት ቀላል ጥፋቶች ብቻ መሆናቸውንና ከባድ ጥፋቶች ግን በወንጀል ሕጉ መሠረት የሚታይ እንደሆነ ሰብሳቢው አመላክተዋል።

ምክር ቤቱም የመረጃ ነፃነት ረቂቅ አዋጅን አዋጅ ቁጥር 1427/2018 አድርጎ በሙሉ ድምፅ አጽድቋል።

በተየያዘም የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ረቂቅ አዋጅን ለማጽደቅ የቀረበውን ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ የሕግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እፀገነት መንግሥቱ ለምክር ቤቱ በንባብ አቅርበዋል፡፡



የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እፀገነት መንግሥቱ የአዋጁን አስፈላጊነትና ይዘት ሲያቀርቡ በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 34 እና 78 በተቀመጠው የግልና የቤተሰብ የሕግ ጉዳዮችን በሃይማኖታዊ ሕጎች ላይ ተመስርቶ በፈቃደኝነት ለመዳኘት ያስችላል፣ የዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነት የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እንደ አንድ የፍትህ አካል የዳኝነት ነፃነታቸው ተጠብቆ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት፣ ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል።

አደረጃጀትና ተጠሪነት ሃይማኖታዊ እሴቶችን የሚያከብረው ይህ አዋጅ የፍርድ ቤቶቹን አደረጃጀት፣ ተጠሪነት እንዲሁም የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ጉባዔን የሚያቋቁም ነው። የምክር ቤት አባላት ረቂቅ አዋጁን ለማዳበር የተደረጉት የምክክር መድረኮች በቂና አሳታፊ እንደነበሩ በሰጡት አስተያየት ገልጸው፣

ምክር ቤቱም ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ረቂቅ አዋጅን አዋጅ ቁጥር 1428/2018 በማድረግ በሙሉ ድምፅ አጽድቋል።

6ኛው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በ5ኛ ዓመት የስራ ዘመኑ ሰኔ 18 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 1ኛ ልዩ ስብሰባው  የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችንና እና የብድር ስምምነቶችን አጽድቋል፡፡

ምክር ቤቱ በውሎው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ለዘላቂ እና ሁሉን አቀፍ የእድገት ልማት ፖሊሲ ማስፈፀሚያ የሚውል የብድር ስምምነት አዋጅ አስፈላጊነት የመንግሥት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ የተከበሩ ወ/ሮ መሠረት ኃይሌ ለምክር ቤቱ ሲያብራሩ ብድሩ፣ መንግሥት በተለያዩ ዘርፎች የጀመራቸውን የኢኮኖሚ ማሻሻያ እርምጃዎች ለማበረታታትና ለመደገፍ እንዲቻል የሚያግዝ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በተየያዘም መንግሥት የአየር ንብረት ለውጥን ለመቆጣጠር የመሬት መራቆትን ለመቀነስና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ አረንጓዴ ስትራቴጂን እየተገበረ መሆኑን አስረድተው፣ ተፋሰስን መሠረት ያደረገ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ልማት ሥራዎች ለምርታነማት መጨመር ሚና እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

ባለፉት ስድስት ዓመታት ሲተገበር የቆየው የማህበረሰብ ተኮር የመሬት አያያዝ ፕሮግራም ያስመዘገበውን ውጤት መሠረት በማድረግ የሁለተኛው ምዕራፍ የማህበረሰብ የመሬት አያያዝ ፕሮግራም መቀረጹን አውስተው፣ በዋናነት በደጋማ አካባቢዎች የመሬት ምርታማነት ለመጨመር የገጠሩ ህብረተሰብ ኑሮ በማሻሻልና የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖ በመቀነስ ረገድ የብድር ስምምነቱ የማይተካ ሚና እንዳለው አብራርተዋል፡፡

እንዲሁም ምክር ቤቱ ለአየር ንብርት ለውጥ የማይበገር የመስኖ ልማት ዘላቂ ምርታማነት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ከዓለም አቀፍ ልማት ማህበር የተገኘውን ብድርም የኢትዮጵያ ግብርና ለአየር ንብረት ለውጥ ያለው ተጋላጭነት ከፍተኛ በመሆኑ የመስኖ ልማትን ለማዘመንና ለማስፋፋት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ወሳኝ መሆኑን ጠቁመው፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር መስኖ ልማት ለዘላቂ ምርታማነት የግብርና ስርዓትን ወደተሻለ ምርታማነት ለማሸጋገር ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ገልፀዋል፡፡

በማስከተልም ረቂቅ የብድር ስምምነቶቶቹ ወደ ሁለተኛ ንባብ ተሸጋግረው ዝርዝር ውይይት ተደርጎባቸው እንዲጸድቁ የተከበሩ ወ/ሮ መሠረት ኃይሌ የመንግሥት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ ጠይቀዋል፡፡

ምክር ቤቱም የብድር ስምምነቶቹ ወደ ሁለተኛ ንባብ ተሸጋግረው እንዲጸድቁ የደገፈ በመሆኑ ዝርዝር ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የዘላቂ እና ሁሉን ዓቀፍ የእድገት ልማት ፓሊሲ ማስፈፀሚያ የሚውል የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1429/2018 በማድረግ በሁለት ድምፅ ታአቅቦ በአብላጫ ድምፅ አጽድቋል፣

በተያየዘም ለሁለተኛው የማህበረሰብ ተኮር የመሬት አያያዝ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1430/2018 በማድረግ በሙሉ ድምፅ አጽድቋል፣

እንዲሁም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የመስኖ ልማት ለዘላቂ ምርታማነት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውሉ የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1431/2018 በማድረግ በመሉ ድምፅ አጽድቋል፡፡

በተያያዘም ምክር ቤቱ የምግብ ሥርዓት እና ሥርዓተ ምግብ ረቂቅ አዋጅ የጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ወርቀሰሙ ማሞ የረቂቅ አዋጁን ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ በንባብ አቅርበዋል፡፡



አክለውም ጥራትና ደህንነቱ የተረጋገጠ የተመጣጠነ ምግብ ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ ማድረግ፣ በሕፃናትና እናቶች ላይ የሚታየውን የሥርዓተ-ምግብ እጥረት ችግር በሕግ ማዕቀፍ በተደገፈ አሰራር በዘላቂነት መፍታት እና በምግብ እሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ሁሉንም ተዋናዮች በቅንጅት ማሳተፍ የረቂቅ አዋጁ ዋና ዋና ትኩረቶች ናቸው ብለዋል።

ምክር ቤቱም በስፋት ከተወያየ በኋላ የአዋጁ መጽደቅ የሀገሪቱን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማፋጠን እንዲሁም የምግብ ደህንነትን አስተማማኝ ለማድረግ ትልቅ ምዕራፍ እንደሚሆን በመገንዘብ የምግብ ሥርዓት እና ሥርዓተ ምግብ ረቂቅ አዋጅን አዋጅ ቁጥር 1432/2018 አድርጎ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል።

የተከበሩ አቶ ሰለሞን ላሌ የረቂቅ አዋጁን አስፈላጊነትና የተካቱትን መሠረታዊ ነጥቦች ለምክር ቤቱ ሲያብራሩ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ የሚያቋቁሙ አምራቾች ለሥራቸው የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለማስገባት የውጭ ምንዛሪ ቅድሚያ እንዲያገኙ እንደሚረዳና የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችን ምርት በአንድ ላይ በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በገበያ ላይ የመደራደር አቅማቸውን ከፍ እንደሚያደርግ አስገንዝበዋል።



የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

አክለውም የግብርና ምርቶች ሳይቀነባበሩ በዝቅተኛ ዋጋ ከመሸጥ ይልቅ፣ እሴት ተጨምሮባቸው ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲቀርቡና የአርሶ አደሩ ገቢ እንዲያድግ እንዲሁም አምራቾች ከተለመደው የአነስተኛ ማደራጃ ዘይቤ ወጥተው ወደ መካከለኛ የግብርና ባለሀብትነትና አልሚነት እንዲሸጋገሩ ህጋዊ ማዕቀፍ የሚፈጥር መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ምክር ቤቱ በቂ ውይይት ካደረገ በኋላ የግብርና ቢዝነስ ኩባንያ ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1433/2018 ሆኖ በሙሉ ድምጽ አድቋል፡፡

6ኛው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በ5ኛ ዓመት የስራ ዘመኑ ሰኔ 23 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው መደበኛ ጉባኤው በፌዴራል መንግሥት በ2019 በጀት ዓመት የበጀት ዕቅድ ላይ ዝርዝር ወይይት ያደረገ ሲሆን ምክር ቤቱ በውሎው የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ አጽድቋል፡፡



የበጀት ዕቅዱ ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ የሰጡት የገንዘብ ሚኒስትሩ ክቡር አቶ አህመድ ሽዴ የ2019 በጀት ዓመት ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የማህበረሰብ ክፍል ከግምት ውስጥ ያስገባና የዜጎችን የመግዛት አቅም የሚያግዝና የኑሮ ውድነትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ለማህበራዊ ወጪዎች

የሚደረግ ድጎማን ከግምት ውስጥ በማስገባት ያካተተ በጀት መሆኑን ገልፀዋል ፡፡ አክለውም ሚኒስትሩ የአገር በቀል ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከግምት ውስጥ ያስገባና የማክሮ ኢኮኖሚ ስብራቶች ለማረም የሚያስችል መሆኑን፣ በአጠቃላይ የ2019 ዓ.ም በጀት በትምህርት፣ በማህበራዊ ጉዳዮች፣ ለጤና፣ ለኢነርጂና መሰል ዘርፎች ትኩረት የሰጠ መሆኑን ለምክር ቤቱ አስረድተዋል፡፡

ምክር ቤቱ በውሎው የፌዴራል ታክስ አስተዳደር ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ፣ የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ ረቂቅ አዋጅ እና የኢትዮጵያ የካርበን ገበያ ረቂቅ አዋጅን ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ የፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ ደሳለኝ ወዳጆ ለምክር ቤቱ በንባብ አሰምተዋል፡፡

ምክር ቤቱ በረቂቅ አዋጆች ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ የፌዴራል ታክስ አስተዳደር ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1434/ 2018 በማድረግ በሁለት ድምፀ ታአቅቦ በአብላጫ ድምፅ አጽድቋል፤

የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1435/2018 ሆኖ በሙሉ ድምፅ ፀድቋል፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ የካርበን ገበያ ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1436/2018 በማድረግ ምክር ቤቱ በአንድ ድምፅ ታአቅቦ በአብላጫ ድምፅ አጽድቋል፡፡

## ክትትል ቁጥጥር

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን ሰኔ 11 ቀን 2018ዓ.ም በአካሄደው 26ኛ መደበኛ ጉባኤው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2017 በጀት ዓመት ሒሳብ የፋይናንሺያል፣ የሕጋዊነት እና የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት አዳምጧል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE





የፌዴራል ዋና ኦዲተር ክብርት ወ/ሮ መሠረት ዳምጤ፣ በበጀት አመቱ በፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤቶች የ2017 በጀት ዓመት የተከናወኑትን የፋይናንስ ህጋዊነት የክዋኔ ኦዲት እና የ2018 ዓ.ም በጀት ዓመት የመስሪያ ቤታቸውን አጠቃላይ አፈፃፀም ሪፖርት ለምክር ቤቱ አቅርበዋል።

በበጀት ዓመቱ ተሰብሳቢ ሂሳብ ከተገኘባቸው ተቋማት መካከል ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የጤና ሚኒስቴር፣ ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ፣ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር፣ የመስኖ ቆላማ እና አካባቢ ሚኒስቴር፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ዋና ኦዲተሯ የ2017 በጀት ዓመት የኦዲት ነቀፌታ የሌለባቸው ተቋማት ከጥቂት ጉድለት ውጭ አጥጋቢ ሆነው የተገኙት ሲሆን በተወሰኑት ላይ አስተያየት መስጠት ያልተቻለባቸው ተቋማት ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸው አምስት ተቋማት መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በፋይናንሽያል ህጋዊነት ኦዲት ነቀፌታ የሌለበት የኦዲት አስተያየት የሚሰጣቸው መስሪያ

ቤቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መምጣታቸውን አመላክተዋል። በመረሻም የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ የሺእመቤት ደምሴ (ዶ/ር) ቋሚ ኮሚቴው የፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤትን አፈፃፀሞች በመገምገም ክፍተቶችን ለይቶ ግብዓት ሲያቀርብ መቆየቱን ጠቁመው፣

በ2017 በበጀት ዓመት ለልማት ሥራዎች የተመደበውን የበጀት ኦዲት ሽፋን ማሳካት መቻሉ፣ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማትና የሰው ኃይል አቅም እየተጠናከረ መምጣቱ፣ ከዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ ማንዋሎች መዘጋጀት መቻሉ የሚበረታቱ መሆናቸው ግብረ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የምክር ቤቱ አባላት በበኩላቸው ተቋሙ የኦዲት ባለሙያዎችን አቅም በማጠናከር የኦዲት ሽፋንን ለማሳደግ ከአስፈፃሚ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሠራርን በይበልጥ ማጠናከር እንደሚገባ የምክር ቤት አባላት አመላክተዋል።

በመጨረሻም የኦዲት ሥራ የብዙ አካላትን ተሳትፎ የሚፈልግ በመሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጀት በመሥራት የኦዲት ተደራሽነት ሙሉ እንዲሆን በትኩረት መሥራት እንደሚገባ የምክር ቤት አባላት አሳስበዋል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የስራ ዘመኑ ሰኔ 16 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 27ኛ መደበኛ ጉባኤው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንን የ11 ወራት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት አዳምጧል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE





የምክር ቤት አባላት ኮሚሽኑ ምርጫውን ከመታዘብ አኳያ ያስመዘገባቸውን ውጤቶች፣ ግጭቶችና አደጋዎች ከመድረሳቸው በፊት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ለመከላከል እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን፣ ከሚቀርቡ አቤቱታዎች የሴቶች ድርሻ ሃያ ስድስት በመቶ ብቻ የሆነበትን ምክንያት፣ እንዲሁም ዜጎች መብቶቻቸውን እንዲያውቁ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ የተሰሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በሚመለከት ከምክር ቤት አባላት ጥያቄዎች አንስተዋል።

የኢትዮጲያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር አቶ ብርሃኑ አዴሎ ተቋሙ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ትብብር በመፍጠር ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሥራ ሲሰራ መቆየቱን ገልፀዋል።

ኮሚሽኑ ከአውሮፓ ሕብረት፣ ከተለያዩ ኢምባሲዎች፣ ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድርጅት አህጉር አቀፍ ተቋማት ጋር ትብብሮችን በማጠናከር የተለያዩ ድጋፎች መገኘት መቻሉን ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ክቡር አቶ ብርሀኑ አዴሎ፣ ኮሚሽኑ በ7ኛው ሀገራዊ ምርጫ በታዛቢነት መሳተፉን ጠቁመው ለምርጫ ታዛቢዎች፣ ለዳኞች እና ለሚዲያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መሠጠቱን እንዲሁም በሴቶች፣ በአካል ጉዳተኞችና በአረጋውያን መብቶች ዙሪያ ልዩ ልዩ ስልጠናዎች መሰጠታቸውን አብራርተዋል።

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችንና ስደተኞችን በተመለከተ፣ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ብሔራዊ ስትራቴጂዎች ተዘጋጅተው እየተሰራባቸው መሆኑን ጠቁመው፣ የተፈናቃዮችን ጉዳይ የተመለከቱ ህጎች እንዲወጡና የሚያስፈጽም አካል በህግ የሚሰየምበት ሁኔታ እንዲኖርና ሌሎች መፍትሄዎች እንዲመጡ ኮሚሽኑ አሳስቧል፡፡

ኮሚሽነሩ አክለውም ኮሚሽኑ ኩነቶችን ለማረጋገጥ የሚጠቀምባቸው መንገዶች ዓለም አቀፍ የምርመራ ስልትን የተከተሉና ደረጃቸውን የጠበቁ በመሆናቸው ተቋሙ የሚያወጣቸው ሪፖርቶች የማያጠራጥሩ መሆናቸውንም ገልፀዋል።

የሴቶችን አቤቱታ በተመለከተ ለተነሳው ጥያቄ የሴቶች ተሳትፎ እየጨመረ መምጣቱን ጠቅሰው፣ ከግንዛቤና ትምህርት አንጻር ለተነሳው ጥያቄም የሰብዓዊ መብት ክበቦችን በማስፋፋትና ሰብዓዊ መብት በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ እንዲካተት በትኩረት እየተሰራ መሆኑን አብራርተዋል።

የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ እውነቱ አለነ በሰጡት አስተያየት፣ ኮሚሽኑ በምርጫው የነበረው የታዛቢነት ተሳትፎ ሀገራችን በራሷ አቅም ምርጫዋን መታዘብ መቻሏ የሚበረታታ መሆኑ፣ ኮሚሽኑ በፖሊስ ጣቢያዎችና በማረሚያ ቤቶች የሚያደርገው ክትትል የሚበረታታ መሆኑን ጠቅሰው፣

በግጭት አውድ ውስጥ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በተመለከተ የሚወጡ ሪፖርቶች ታማኝነታቸውን በሚገባ ማረጋገጥና በጥንቃቄ መከወን የሚገባው መሆኑ እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ራሱን የቻለ ተቋም እንዲኖር የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አሳስበዋል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

## የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የስራ ዘመኑ ሰኔ 18 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 28ኛ መደበኛ ጉባኤው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት አዳምጧል።






በቀረበው ሪፖርት ላይ የምክር ቤት አባላት ከካሳ ክፍያ ሥርዓት፣ ከመረጃ ነፃነት እና በግል ተቋማት ሊፈጠሩ የሚችሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ቀድሞ ለመከላከል የግንዛቤ ሥራዎች በስፋት ሊሰሩ እንደሚገባ፣ ተቋሙ ተደራሽነቱን በማስፋት ወደ ሁሉም ክልሎች ተደራሽ ማድረግ እንደሚገባው ጠይቀዋል፡፡ ሪፖርቱን ለምክር ቤቱ ያቀረቡት የተቋሙ ዋና እንባ ጠባቂ ወ/ሮ ስመኝ ውቤ እንደገለጹት፣ ተቋሙ በሕግ የተደነገጉ የዜጎች መብቶችና ጥቅሞች በአስፈፃሚ አካላት እና በግል ድርጅቶች መከበራቸውን የማረጋገጥ ሥራ እየሰራ ይገኛል።

በዚህም የሕግ የበላይነት፣ ግልጽነትና ቅልጥፍና የሰፈነበት መልካም አስተዳደር እንዲሁም የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲመጣ ዓላማ አድርጎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን አስረድተዋል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝበ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

አክለውም ተቋሙ በማህበረሰቡ ውስጥ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ በሕፃናት፣ በሴቶች፣ በአረጋውያን እና በአካል ጉዳተኞች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አስተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከል ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የምክር ቤት አባላት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የዜጎችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለማስጠበቅ የጀመራቸውን ሥራዎች አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል፡፡



በመቀጠልም የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ እውነቱ አለነ ተቋሙ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና አስተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከል የሚያደርገውን ክትትል አጠናክሮ እንዳለበት፣ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመቀመርና የዲጂታል አሰራርን በመጠቀም በዜጎች ላይ የሚደርሱ በደሎችን ቀድሞ መከላከል መቻል እንደሚገባ፣ ተቋሙ ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ የሕፃናት፣ ሴቶች፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራቱ መቻሉ፣

ተቋሙ በበጀት ዓመቱ በ108 የመንግሥት ተቋማት ላይ ክትትል ለማድረግ አቅዶ፣ በተሻለ አፈጻጸም በ201 መሥሪያ ቤቶች ላይ ቁጥጥር መቻሉ፣ የዲጂታል አሠራርን በማዘመን ዜጎች ባሉበት ሆነው በነፃ ጥሪ ስልክ መስመር በ9503 አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉበት ሥርዓት መዘርጋቱ መቻሉ የሚበረታታ መሆኑ አመላክተዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝበ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

## ለበለጠ መረጃና አስተያየት

### አድራሻ (Address)

ስልክ Tel:- 011-13-49-70
ነፃ ስልክ ጥሪ Free call 8557
ፖስታ ሳጥን ቁጥር P.O.Box : 80001
ኢ..ሜይል E-mail info@hopr.gov.et

በኢ.ፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት የኮሙኒኬሽን፤ አስተህምሮና ሙዚየም መሪ ሥራ አስፈፃሚ የተዘጋጀ፤